# የACPS Express 3/17/2023: አራት የእርዳታ-ሰጪ ሠራተኞች - እንደ የ‘VIP’ ሽልማት-ተሸላሚ ሆነው - መመረጣቸውን፤ ACPS አስታውቋል

## አራት የእርዳታ-ሰጪ ሠራተኞች - እንደ የ‘VIP’ ሽልማት-ተሸላሚ ሆነው - መመረጣቸውን፤ ACPS አስታውቋል



በቅርብ-ጊዜ የሁለተኛውን - ዓመታዊ የ‘Vision, Integrity and Passion (VIP)’ ተቀባይ-የሆኑት፣ ተቀጣሪ-ሠራተኞች እውቅናን-አግኝተው ተመርጠዋል። የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፣ በሚከተሉትን ምድቦች-ውስጥ - በእርዳታ-ሰጪ ሠራተኛ/support staff፣ ይህም የሚያካትተው በማዕከላዊ ቢሮ እርዳታ ሰጪዎችን፣ በህንፃ-ደረጃ እርዳታ ሰጪዎችን፣ የአስተዳደራዊ እርዳታ-ሰጪዎችን፣ የACPS ትተቆጣጣሪዎችን እና የትምህርት ቢእት የጥበቃ ቁጥጥር አድራጊዎችን ያካተተውን - የ2022-23 ሽልማት-ተሸላሚዎችን ሲያሳውቅ-ኩራት ይሰማዋል።

- ካሶንያ ሊ (Casonja Lee)፣ የአስተዳደራዊ ባለሞያ - በአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት- ኪንግ ስትሪት ካምፓስ (King Street Campus
- ማሪአ ፖርቲሎ (Maria Portillo) - የጥበቃ-ሠራተኛ - በአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት- ኪንግ ስትሪት ካምፓስ (King Street Campus
- ሊንዳ ሮድሪገዝ (Linda Rodriguez)፣ የአስተዳደራዊ ባለሞያ - በACPS የማህበረሰብ አጋርነቶች እና ተሣትፎ ቢሮ (Office of Community Partnerships and Engagement)።
- ሼሪ ስተፈንስ (Sheree Stephens)፣ የአስተዳደራዊ ባለሞያ - በአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት- ሳተላይት ካምፓስ (Satellite Campus)።




ካሶንያ ሊ (Casonja Lee)፣ ለACPS ለ31 ዓመታት ያገለገሉ እና በእጅጉ-የተከበሩ የሠራተኛ-አባል ናቸው። ሊ (Lee)ን በእጩነት በመምረጥ ውስጥ፤ የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School) - ኪንግ ስትሪት ካምፓስ (King Street Campus) (ACHS) ካውንስለር የሆኑት - ዲ ማራራ (Dee Marrara) እንዳሉት፤ “በ‘መደበኛ’ ስራዎቿ ቀልጣፋ፣ መረጃ-ያለው እና እርዳታ-መለገስ የምትችል ብቻ ሳትሆን፣ ከሌሎች ተማሪዎቻችን ጋር ባላት ግንኙነቶች አኳያ ከሚገባው በላይ እየሄደች የምትሰራ-ናት። ሚ/ስ ሊ (Ms. Lee)፤ ኮስታራ-ናቸው፣ ግን ደግሞ አፍቃሪ እና ሁሉም በአግባቡ-አድራጊ ናቸው።” ማራራ

(Marrara) እንዳሉት፤ ሊ (Lee) - በክፍለ-ጊዜዎች መካከል ተማሪዎችን በመተላለፊያ/hallway ለማገዝ - ሁልጊዜ እዚያ-ትገኛለች። “በአስቸጋሪ-ሁኔታ የተሸፈነን ሳይቀር የሚከፍት፣ ግሩም የሆነ የተጫዋችነት ችሎታ (sense of humor) አላት።”



ማሪአ ፖርቲሎ (Maria Portillo) - በእያንዳንዱ ቀን የACHS - ዓለም-አቀፍ አካዳሚ (International Academy (IA) ተማሪዎችን ለመርዳት እና ለመጠበቅ ትሠራለች፤ እና በ‘ACHS’ ውስጥ በሦስተኛው ፎቅ ላይ እንደ “the rock” ተብላ-ትታወቃለች። ወደ 20 ዓመታት ከሚጠጋው አገልግሎቷ ጋር፣ ሁልጊዜ-ወጥነት ያላት፣ ጠንካራ እና ለሁሉም እኩል በሆነ ከተማሪዎች-ጋር ግንኙነት እንዳላት ይታወቃል። “በስም-ታውቃቸዋለች፣ እና በክፍል-ውስጥ ትንከባከባቸዋለች። በ‘IA’ ውስጥ የአዳራሹ ተቆጣጣሪ ሆና ከእኛ-ጋር በመስራቷ - ወርቅ አስገኝታናለች፤” ብለዋይ የ‘IA’ አስተማሪ ፓትርሺአ ጎርደን (Patricia Gordon)። “በአካባቢዋ የሚገኙትን እንዴት ባለሞያተኛ መሆን-እንደሚችሉ እና ተማሪዎች በዙሪያዋ የደህንነት-ስሜት እንዲሰማቸው የምታነቃቃ ነች፤” በማለት - የእንግሊዘኛ ቋንቋን የሚማሩ (English Learner) አስተማሪ ሚጃል አልትማን (Mijal Altmann) ጨምረውበታል። የ‘IA’ ረዳት ርዕሰ መምህር - ሚሼል ካምፒግሊአ (Michelle Campiglia) በመጨመርም፤ ፖርቲሎ (Portillo) በመምረጥ-ሲያቀርቡ እንዳሉት፤ በስራዋ በጣም-አስደናቂ ናት፣ ብለዋል። “ቋሚ በሆነው መገኘታቸው፣ ከተማሪዎች ጋር ባላቸው አዎንታዊ ግንኙነቶች፣ እና ከሠራተኞች እና አስተዳደር ጋር ትብብርን-ለማድረግ ባሳዩት ፈቃደኝነት አማካኝነት፤ ዓለም-አቀፍ አካዳሚ (International Academy)ን በቋሚነት-የረዱ ናቸው።”



ሊንዳ ሮድሪገዝ (Linda Rodriguez) - ACPS ከ27 ዓመታት በላይ ያገለገሉ እና፣ ለቢሮዋቸው እና ለአጠቃላይ ክፍሉ/division ስኬታማነት - ዋነኛ-መሆናቸውን፤ በማህበረሰብ አጋርነቶች እና ተሣትፎ ዋና ዳይሬክተር - ከርት ሆፍማን (Kurt Huffman)፣ አድናቆት-ተሰጥቷቸዋል። “ሚ/ስ ሮድሪገዝ (Ms. Rodriguez)፣ ባለብዙ-ችሎታ ያላቸው፣ ቁርጠኝነት ያላቸው የቡድን-አባል ናቸው፤” ሆፍማን (Huffman) በእጩነት ሲመርጧቸው እንደተናገሩት። “ለአጋሮቻችን እና ለሰው-ሃይል ተሳትፎዎች - እንደየአስፈላጊነቱ መመሪያን እና እርዳታን ይሰጣሉ። ከቡድን አባላቶች ጋር ጠንካራ ግንኙነትን መፍጠር - ለፕሮግራሙ ስኬት አስፈላጊ-መሆኑን ያውቃሉ።” ሲንዲ ሴንቴኖ (Cindy Centeno) - የውጪ ግንኙነት ባለሞያተኛ የሆኑት ጨምረው-ሲናገሩ፤ “በACPS ላይ ስፋት እና ጥልቀት-ያለው እውቀታቸው - ስራዬን በይበልጥ ታሪካዊ በሆነ መንገድ ለመቅረብ-ማድረግ፣ እና እንደ-የስራ-ጓደኛነት ከእርሷ ጋር የስራ-ጊዜዬን ለመጋራት-በመቻሌ ደስተኛነት-ይሰማኛል።” የትምህርት ቤት እና የማህበረሰብ ግንኙነቶች ሹም የሆኑት ጁሊአ ቡርጎስ (Julia Burgos) እንዳሉት፤ “ሚ/ስ ሮድሪገዝ (Ms. Rodriguez)፣ ራዕይ፣ ታማኝነት እና ታላቅ-ስሜት ያለው የሠራተኛ-አባል ለመሆን ምን-እንደሚጠይቅ አንጸባራቂ ማሳያ-ምሳሌ ናቸው። በፋይናንስ ጠቢብ የሆኑ እና ሠራተኞች ትክክለኛ እና ሕጉን-ተገገር ሆነው - ታማኝነትን ላይ እርዳታ-በማድረግ፤ ያላቸውን ልዩ የችሎታ-ልምዳቸውን የሚያጋሩ-ናቸው። በሁሉም ስራቸው እና አገዛቸው አማካኝነት፤ በደንብ-በሚሰራውን መሣሪያ እና ቀልጣፋ-የሆነ መምሪያ ውስጥ የሚመጣ፤ ራዕይ-አላቸው።



ሼሪ ስተፈንስ (Sheree Stephens)፤ ‘GOAT’ — የጊዜያችን-ምርጥ የሆኑ — እና የACHS-ሳተላይት ካምፓስ/Satellite Campus - የልብ-ትርታ፤ ተብለው የሚጠሩ-ናቸው። ወደ 25 ዓመታት የሚጠጋ በACPS ውስጥ ካላቸው ግልጋሎት ጋር፣ ስተፈንስ (Stephens)፤ ተማሪዎችን፣ ቤተሰቦችን እና ሠራተኞችን በመደገፍ የሚችሉትን ሁሉ በማድረግ የታወቁ-ናቸው። “ግሩም-የሆነ የማስታወስ-ችሎታ አላቸው እና ስለተማሪዎች እና ቤተሰቦች ትናንሽ-ዝርዝሮችን ሳይቀሩ ያስታውሳሉ፤ ይህን መረጃ የአስተማሪዎችን እና የካውንስለሮችን ጣልቃ-ገብነቶችን ለመምራት ይጠቀሙበታል፤” ብለዋል የሳተላይት (Satellite) ትምህርት ቤት ካውንስለር ክርስቲን ኒል (Kristin Neil)። “በህይወቴ ከማውቃቸው በይበልጥ-ቅንብር-ያላቸው (organized) ሰዎች መካከል አንዷ-ናት፤ በዚህም ተወራርጄም ተሸንፌ-አላውቅም። ሃዘኔታ-የሚሰማት፣ አስተዋይ እና ችግሮችን የመፍታች ችሎታ ያላት ናት።”

## ማይክል ኤ. ዲጊንስ (Michael A. Diggins) እንደ - የተማሪ አገልግሎቶች (Student Services) ዋና ዳይሬክተር ሆነው-መሾማቸውን፤ ACPS አስታውቋል



ማይክል ኤ. ዲጊንስ (Michael A. Diggins)፤ እንደ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - የተማሪ አገልግሎቶች (student services) ዋና ዳይሬክተር ሆነው የተሾሙ፣ እና የስራ-ድርሻቸውን - ከኤፕሪል (April) 10 ቀን 2023 ጀምሮ-ይቀጥላሉ። በዚህ-የስራ ድርሻ፣ ዲጊንስ (Diggins)፤ የተማሪ አገልግሎቶች (Student Services) ቢሮን የበላይ-ተቆጣጣሪ በመሆን - ከፍተኛ ደረጃ ያለው የቁጥጥር እና ግምገማ ሂደትን፣ የተጠያቂነት እና እርዳታን በማካሄድ - የዕለት-ተዕለት ክንውኖችን በመምሪያው ውስጥ የሚያከናውኑ ሠራተኞችን በማሰማራት-ይሠራሉ።

“ሚ/ር ዲጊንስ (Mr. Diggins)፣ ለACPS -ተመሳሳይነት-የሌለውን የቁርጠኝነት-ደረጃ የሚያመጡ ናቸው። ባለፉት 28 ዓመታት በላይ ሆን-ተብሎ ከተማሪዎች እና ከቤተሰቦች ጋር የገነቡትን አሁን-ያለውን ግንኙነቶች፤ ልዩ-ከሆነው ችሎታቸው ጋር አጋር-ሆኖ እና ጥቅል-የሆነውን እውቀታቸውን ተጠቅመው፤ ለዚህ-አዎታዊ የሆነ ፈጠራዊ-ስራዎች ለማምጣት የሚያስችላቸው መሆኑን፤” ብለዋ የተማሪ አገልግሎቶች እና ፍትሃዊነት (Student Services and Equity) ዋና ሹም - ዶር/ ማርሲአ ኢ. ጃክሰን (Dr. Marcia E. Jackson)። “ለተማሪዎቻችን በይበልጥ አዎታዊ-የሆነ መንገዶችን በማስገኘት ከትምህርት ቤት ሠራተኞች ጋር በአጋርነት-በመስራት - ወደ ‘የተማሪ አገልግሎቶች እና ፍትሃዊነት-እኩልነት (Student Services and Equity) ቡድን ውስጥ አብረው-እንዲቀላቀሉ በጉጉት-እንጠባበቃለን።”

ዲጊንስ (Diggins) - መጀመሪያ ወደ ACPS የተቀላቀሉት በ1995 ሲሆን፤ በቅርብ-ጊዜ ደግሞ እንደ ዋና አስተዳደር ለክንውኖች እና ተማሪ እርዳታ - ሆነው ፤ በአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት- ኪንግ ስትሪት ካምፓስ (King Street Campus) ውስጥ አገልግለዋል። ዲጊንስ (Diggins)፤ ተማሪዎችን ጉልበት-በመስጠት እና በከፍተኛ ትምህርት ዲፕሎማ፣ ኮሌጅ እና የስራ-መስኮች ላይ በርካታ-መንገዶች እንዳላቸው ለማረጋገጥ - በጥንካሬ-ይሰራሉ። ውጤታማ-ለመሆን ክፍተቶችን ከሚፈጥሩ ነገሮች-መካከል፤ በማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ እና የቀለም ትምህርት (Social, Emotional, and Academic Learning (SEAL) - ለተማሪ አስፈላጊ-የሆነውን እርዳታ ለማስገኘት ትኩረት እያደረገ-ባለበት ጊዜ፤ በቂ-በሆነ ሁኔታ አገልግሎት-ያላገኙትን ተማሪዎችን ለመርዳት፤ ሠራተኞችን መርተዋል።

በACPS በነበራቸው የስራ-ጊዜ ውስጥ፣ ዲጊንስ (Diggins) - እንደ የተማሪ ዲን (dean) ሆነው - በመካከለኛ እና በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደረጃዎች ላይ፤ እንዲሁም - ተባባሪ ርዕሰ መምህር ሆነውም አገልግለዋል። በመጀመሪያ እንደ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት - የቴክኖሎጂ አስተማሪ ሆኖ ወደ ክፍሉ/division የተቀላቀሉ እና፣ በመቀጠልም እንደ ግብይት እና የቀውስ/crisis የመረጃ-ምንጮች አስተማሪ ሆነው-አገልግለዋል።

ዲጊንስ (Diggins)፤ የባችለር ዲግሪያቸውን በግብይት ትምህርት (Marketing Education) - ከቨርጅኒያ ቴክ/Virginia Tech ያገኙ፣ እና የማስተርስ ትምህርትን - በትምህርት አመራርነት - ከጆርጅ ሜሰን ዩኒቨርስቲ አግኝተዋል። በቨርጅኒያ ቴክ (Virginia Tech)፣ በ'Integrating Standards of Learning in Curriculum' የተመራቂ-ሰርተፊኬትን አግኝተዋል። በተጨማሪም፤ ከጆርጅ ሜሰን ዩኒቨርስቲ (George Mason University) በትምህርት ቤቶች 'Integration of Technology' ሰርተፊኬት አላቸው። ከቨርጅኒያ ድህረ-ምርቃ ፈቃድ-መስጫ - በትምህርት አስተዳደር የ'post-grad K-12'ንም የያዙ-ናቸው።

## ከ6-12 ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ-ተማሪዎችን መቅረቶችን/Absences፣ ለቤተሰቦች የሚያሳውቅ - አዲስ የ'ACPS Procedures'




ተማሪዎች በመማሪያ-ክፍላቸው ውስጥ የሚያሳተፉበትን-ጊዜ ለማራዘም በምናደርገው-ጥረቶቻችውን ውስጥ፤ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - ከ6-12 ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎቻች ላይ በስራ-ላይ የሚውል - ስለ አዲስ ሂደት የሚገልጸውን፤ ለቤተሰቦች እያስታወቀ-ነው። ይህን አዲስና ማሻሻያ (update) - ስለ ተማሪ መቅረቶች/absences ቅድሚያ ማስታወቂያ - በማርች (March) 13 ቀን 2023 ላይ ተፈፃሚ የሆነው ማጋራት እንፈልጋለን፤ እንደ ተጨማሪ ሆኖ - [በመቅረት/absenteeism አዲስ ቪዲዮ] ላይም ቀርቧል።

በሁለተኛ-ደረጃ (ከ6-12 ክፍሎች) ውስጥ፣ ከመጀመሪያ የክፍል-ጊዜው በኋላ እና በምሣ-ሰዓት ላይ - ተማሪያቸው ቀሪ-ሆኖ ተመዝግቦ እንደሆነና እንዳልሆነ፤ በዚያኑ የትምህርት ቀን ውስጥ - ወላጆች/አሳዳጊዎች እንዲያቁት-የሚያደርግን - አዲስ ሂደትን - ACPS በስራ-ላይ አውሏል። አስተማሪዎች፤ በሁሉም የክፍለ-ጊዜው ወቅቶች ውስጥ - በትምህርት-ገበታ መገኘት/attendanceን ይወስዳሉ። የኢሜል እና ቴክስት/text ማስታወቂያዎች፤ ወላጅ/አሳዳጊ በሚመርጠው ቋንቋ - በ[ParentSquare] ላይ እንደሚከተለው - የሚላክ-ይሆናል:

- ከመጀመሪያ የክፍሉ-ጊዜ ላይ የተደረጉ መቅረቶችን/absences፤ ከመጀመሪያ የክፍሉ-ጊዜ በኋላ፣ በዚህ በጠዋቱ ጊዜ ውስጥ ተማሪያቸው እንደሚጠበቀው በትምህርት ቤት ውስጥ ከሌለ - ወላጆች/አሳዳጊዎችን ለማሳወቅ - አስተማሪዎች ሪፖርት የሚያደርጉበት ነው።

- ከምሣ-ሰዓት በኋላም፤ ማንኛውም ሪፖርት የተደረጉ መቅረቶች/absences - በዚህ የትምህርት ቀን ሰዓት-ላይ ተፈጽሞ ከሆነ፤ ማስታወቂያዎችን ለወላጆች/አሳዳጊዎች የሚልከም-ይሆናል።
- አሁንም-ቢሆን መደበኛ-የሆነውን የመቅረት ማስታወቂያውን - ተማሪው ከ2 p.m. በኋላ ከትምህርት ቤት ቀሪ-መሆኑ ሪፖርት ከተደረገ - ወይም ቀደም-ካለው ክፍሎች ውስጥ ከ22 p.m.በኋላ ከገባ፤ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ በ6p.m. ላይ በእያንዳንዱ-ቀን ላይ ያገኛሉ፤ (ማስታወሻ: ተማሪው ከሦስት የክፍል-ጊዜዎች በላይ ካመለጠው-እና ክፍል-ካልገባ፤ ይህ እንደ ሙሉ-ቀን መቅረት/absence ሆኖ ሪፖርት-ይደረጋል።)

ይህ ቀደም ብሎ ማስታወቂያ-የሆነው፤ ከ6-12 ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የመጀመሪያውን ክፍል-ጊዜን በክፍል-አለመገኘታቸውን ወይም በቀኑ-አጋማሽ ላይ መቅረታቸውን ሪፖርት በሚያደርግ ጊዜ፤ ወላጆች/አሳዳጊዎች ተማሪው የት-እንዳለ ለመፈለግ ያስችላቸዋል። እነዚህን መረጃዎች ወቅቱን-በጠበቀ ሁኔታ ማግኘት መቻልም፤ ከመቅረት እና ከማርፈድ ጋር የሚገኙ-የተማሪዎች ማንኛውንም ጉዳዮች ላይ፤ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ከACPS ጋር አጋርነትን ፈጥረው ምላሽ-ለመስጠት ይረዳቸዋል።

እንደ-ማስታወሻ ሆኖ፤ የACPS ትምህርት ቤቶች - ዝግ-የሆኑ ካምፓሶች (closed campuses) ናቸው፤ ይህም ማለት - በትምህርት-ቀኑ ውስጥ፣ የትምህርት ቤቱን ግቢ ለቅቆ-መሄድ አይፈቀድላቸውም ማለት-ነው። ተማሪዎች፤ ትምህርት ቤቱን ለቅቀው-መሄድ የሚችሉት - ከወላጅ/አሳዳጊ ወደ ትምህርት ቤት አስተዳደሩ የቀረበት ማስታወሻ ከኖረው ብቻ ፈቃድ-በማግኘት ይችላል። እያንዳንዱ ትምህርት ቤት፤ ፈቃድ-የማግኛ ሂደቱን ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር ያጋራሉ። በትምህርት ቀኑ ውስጥ፤ ተማሪዎቻችን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሆነው እና ትኩረት አድረገው መማራቸው ወሳኝነት-አለው። ACPS፤ በመደበኛነት በትምህርት ገበታ-ላይ መገኘትን በጥብቅ-ትኩረት ይሰጠዋል፤ ምክንያቱም የአንድ-ቀን በክፍል-ውስጥ ያለመገኘት በመማር-ላይ እንቅፋቶችን ሊፈጥር ስለሚችል-ነው።

ይህን በመቅረት/absenteeism ላይ ያሉት ችግሮች ላይ መፍትሄ ከመውሰድ-በተጨማሪ፤ የራሳችን የ'ACPS' ተማሪዎች ከሆኑት ጋር - በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት እና በትምህርት ቤት በሰዓቱ የመድረስን ጠቃሚነት የሚያሳዩ ተከታታይ-ቪዲዮዎችን ለማዘጋጀት - አጋርነትን ፈጥሯል። በተከታታይ-ዝግጅቶቹ/series ውስጥ የመጀመሪያው ቪዲዮ - በኦንላይን መታየት ይችላል። እባካችሁ፤ ይህን ቪዲዮ ከልጃችሁ ጋር ሆናችሁ የመመልከት ዕድልን ብታገኙ፤ ተማሪዎችም ከዚህ ጠቃሚ-የሆነ መልዕክቶችን ማግኘት እንዲችሉ-ያደርጋቸዋል።

ቤተሰቦች - ከተማሪዎቻቸው ጋር እባካችሁ-እንድትነጋገሩ፤ እና በትምህርት ቀኑ ውስጥ፣ ትምህርት ቤት አለመግባት ወይም ትምህርት ቤቱን ካለፈቃድ ለቅቆ-መሄድ - ሊያስከትልባቸው የሚችለውን ቅጣት - መገንዘባቸውን እንዲያረጋግጡ-እንጠይቃቸዋለን። ቤተሰቦች ስለመረጃው - በኦንላይን ላይ ማግኘት ይችላሉ፤ ይህም ስለ the የACPS በግዳጅ-ከደረግ ያለበት (compulsory) በትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘት (attendance) ፖሊሲ እና አዎንታዊ የሆነ በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (attendance) እና አርፋጅነትን/truancy መከላከያ - የመረጃ-ምንጮች (resources) መገኘት-ይችላሉ። በተጨማሪም፤ ወላጆች/አሳዳጊዎች - ከትምህርት ቤት ሬጅስትራር ጋር - በአሁኑ-ጊዜ የሚጠቀሙባቸው የመገኛ-አድራሻዎች ጊዜውን-የጠበቁ በማድረግ፤ — የሞባይል (cell phone) ስልክ ቁጥር እና የኢሜል አድራሻቸው ተስተካክሎ-መኖሩን በማረጋገጥ — የሚላኩላቸውን ማስታወቂያዎች ማግኘት-ይችላሉ። የኦንላይን መረጃውም፤ የParentSquare አፕ/appን ዳውንሎድ/download ለማድረግ ለሚፈልጉ የACPS ቤተሰቦችን የሚገኝ-ይሆናል።

ተማሪዎችን በመማሪያ-ክፍል ውስጥ ለመጠበቅ እና በመማር ሂደታቸው ላይ በየቀኑ ትኩረት-እንዲያደርጉ በምናደርገው-ጥረታችን ውስጥ፤ ከቤተሰቦች እና ከማህበረሰብ የሚደረገውን ትብብር እና እርዳታ ጋር ያለንን አጋርነትና ትብብር እናደንቃለን።

# ለ‘Women’s History Month’ - የተማሪ ስፖት-ላይት/Spotlight: የACHS - ‘Future Club’ ሴቶች



‘Women of the Future (WOTF)’፤ እንደ የተማሪዎች አንድ-አካል ሆኖ በአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) ውስጥ - የአንድን ሰው ድምጽን ለማሳወቅ እና ለውጥን ለማንጣት ጥቅም-ላይ ለማዋል - ስለ ሴቶች መብቶች ግንዛቤን ለመፍጠር ዓላማ-ያለው ነው።  በ2020 ላይ የተመሠረተው ይህ ክለብ፤ በCOVID-19 ወረርሽኝ ምክንያት - አንዳንድ ተማሪዎች -ያጧቸው የመሰላቸውን ትርጉም-ሰጪ ውይይትን እና ግንዛቤን አስፈላጊነት ምላሽ-ለመስጠት የተቋቋመ-ነበር። ተጠባባቂ-ፕሬዚዳንቶች - ሣራ ፕሪንስ (Sara Prince) እና ኦሊቪአ ክሩስ (Olivia Kruse)፤ የከፍተኛ-ደረጃ ተማሪዎች ጉልህ-የሆነ ጊዜያቸውን - ለወደፊት-በመዘጋጀት እና፣ በክለብ አማካኝነት፣ ሴቶች በመንገዳቸው ላይ የሚጋፈጧቸውን ችግሮች ምላሽ-በመስጠት ላይ ትኩረት በማድረግ እንደሚያሳልፉ ተገንዝበዋል።

“የ2020-21 የትምህርት ዓመትን ያሳላፉት፤ የእነዚህ ሴት-ልጆች ውይይቶችን በማሳደግ፣ ከእኩዮቻቸው ጋር የሚያሳትፋቸውን፣ አስቸጋሪ በሆኑ ርዕሶች ላይ በማተኮር - የእርስ-በርስ ትምህርታቸውን እያዳበሩ ባሉበት ጊዜ ተመልክቼአቸዋለሁ፣” ብለዋል የ‘WOTF’ ክለብ አድቫይዘር እና የንግድ እና መረጃ ዘዴዎች አስተማሪ - ጄሲካ ሼፕ (Jessica Schipp) - ሚ/ስ ጄስ (Ms. Jess) ተብለው-የሚታወቁት ሲናገሩ። “ከመጀመሪያው ስብሰባ በኋላ፣ ወደ 30 አካባቢ የሚሆኑ ሴት-ልጆች በርቀት/virtually ከተሰበሰቡ በኋላ፤ ልዩ-የሆነ ነገር እንዳላቸው አውቄ-ነበር። ትምህርት ቤት ወደ በአካል-ተገኝቶ መማር በሚመለስበት ጊዜ ውስጥ፤ ይህ አቀማመጥ በአዲሱ አካባቢ ውስጥ እንዴት-ጥቅም ላይ ማዋል-እንደሚቻል - ሳራ (Sara) እና ኦሊቪያ (Olivia) ለማወቅ-ሲሰሩ እንደነበር ተመልክቼአለሁ።

በመካሄድ ላይ ባሉት በስብሰባው ላይ ውይይት-የተደረገበት ርዕስ እንዴት በተከፋፈለው-ክፍሎቹ ውስጥ — የማህበራዊ ጎራዎች የሆኑት እንደ ዘር፣ ፆታ፣ እና የኢኮኖሚ ሁኔታዎች እርስ-በርስ እንደሚገናኙ — እና ችላ-ሊባሉ እንድሚችሉ ተወያይተዋል። “እኛ ያለው የተከፋፈለው-ክፍሎቻችን፤ እንደ ብሄረሰብ (ethnicity)፣ ማህበራዊ-ኢኮኖሚ ሁኔታ እና ትምህርት፤ እንዴት ሴትነት ለእያንዳንዱ ሰው ልዩ ስለመሆኑ ውይይቶችን የሚያመጣ-ነው፤” ብለው ገልጸዋል ፕሪንስ (Prince)።

የፍትሃዊ-እኩለት ስጋቶች፤ ሴቶች ላይ ተጽዕኖ በሚያደርገው ላይ - ምላሽ-የተሰጠበት ሌላ ዘርፍ-ነው። ፕሪንስ (Prince) በነጥብ-አስመርኩዘው ሲናገሩ፤ በቅርብ-ዓመታት ውስጥ - በሴቶች ላይ - በተለይ ደግሞ ቀለም-ያላቸው (color) - አሁን በስራ-ቦታ ላይ ያሉትን እንቅፋቶች እየተዋጉ ያሉትን በመወከል-ላይ ቁጥሩ-መጨመርን ተመልከተናል። “እኔ እንደማስበው፣ ወደዚህ የፍትሃዊ-እኩልነት ክፍተትን የማጥፋት ስራው የሚጀምርበት ዕድል የሚገኘው፤ በትምህርት ቤት ውስጥ እያለን እና እንደሴትነት በዘመናዊው ማህበረሰብ ውስጥ የየግል-ማንነታችንን እየፈተሸን ባለንበት ጊዜ ውስጥ እንደሆነ አስባለሁ።” በትምህርት ቤት ፕሮግራሞች እና በትምህርት ቤት ክለቦች አማካኝነት - በወንዶች የበላይነት የተያዙ የስራ-መስኮችን - ታዳጊ ወጣት ሴቶች እንዲፈትሿቸው እድሎችን እንዲያገኙ ሃሳብ-አቅርበዋል።

በ‘ACHS’ ውስጥ፣ ፕሪንስ (Prince) ባቀረቡት ማስታወሻ፤ በሣይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስና እና ሂሳብ (Science, Technology, Engineering, and Math (STEM) መስኮች ውስጥ - በSTEM Club ውስጥ ሴቶችን መደገፍን-ጨምሮ፤ የበለጠ ሴቶችን እንዲወከሉ ማድገግን እንዲገፋበት አስታውሰዋል። በመጨመርም-ሲናገሩ፤ “ፈጠራዊ-የሆነ ወደ ‘STEM-based’

ክፍሎች ላይ የሚደረግ አቀራረብ - ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ ቢሆን፤ በበቂ-ሁኔታን አለመወከልን ምላሽ-በመስጠት - ጥቅም-ሊያስገኝ ይችላል፤ ብለዋል። ለተማሪዎች አሣታፊ የሆነ አካባቢን መፍጠር፣ በእነዚህ መስኮች ዙሪያ ስኬትን-እንዲያገኙ - ቁልፍ-የሆኑ መረጃዎችን ለመማር እንዲችሉና - ወደ እኩልነት - መጓገዣው የመጀመሪያ እርምጃ ነው።

'WOTF' - አሉታዊ-የሆነ ሁሉንም በአንድ-ጎራ ከመመልከት (stereotypes) ጋር ከሴትነት ጋር ግንኙነት ያላቸውን - በማስወገድ-ለመርዳት የሚፈልግ ሲሆን፤ ሴቶችን ማካተት ብቻ - ግልጽ-አያደርገውም። ፕሪንስ (Prince) በማስታወስም-ሲያቀርቡ፤ "ምንም እንኳን ግባችን የፆታ እኩልነትን የሚያበረታታ ቢሆንም እንኳን፤ አንዳንድ-ጊዜ እንደ "አክራሪ/radical' ተብለውን ልንፈረጅ የምንችል-ያደርገናል። አጋር ወንድ ተጓዳኞቻችን - በአሁኑ ጊዜ ስለሚገኙት ሁኔታዎች ትምህርት-ያገኙ እና ግንዛቤ ያላቸው መሆናቸው በጣም-አስፈላጊ ነው።"

የተማሪ ክለቡ፤ ታዳጊ-ወጣት ሴቶችን ለማነሳሳት - አርአያ-የሚሆኗቸው መኖራቸው ጠቃሚ-እንደሆነ ያምናል። በወረርሽኙ-ወቅት፤ 'WOTF'፣ ከተለያዩ - በሕግ፣ በግብይት፣ በፖለቲካ፣ ቴክኖሎጂ እና በትምህርት የስራ-ድርሻ የባለሞያተኝነት የመነሻ-እውቀቶች ያላቸውን - በርካታ ተጋባዥ ተናጋሪ እንግዶች ጋር - በመሆን የዙም/Zoom ስብሰባዎችን አዘጋጅቶ-ነበር። እነዚህ ሴቶች፤ የተሳሳቱ-አመለካከቶችን፣ ሴቶችን-መጥላት እና ጭፍን-ጥላቻ ላይ እንዴት በመዳሰስ ለመነጋገር እንደቻሉ - ማዳመጥ-መቻል ጠቀሚታ-ያለው ሆኖ ቡድኑ አግኝቶታል።

የ'WOTF' ተጠባባቂ-ፕሬዚዳንቶቹ እንደሚሰማቸው ከሆነ፤ "ሁሉንም-ነገር ልታገኙ ትችላላችሁ" የሚለው አስተሳሰብ በእያንዳንዱ-ሰው ላይ ከፍተኛ-ጫናን የሚያደርግ ነው - በተለይ ደግሞ በሴቶች ላይ። "ለሴቶች፤ በትምህርት ቤት ወይም በስራ - ፍፁም-ለመሆን ያለባቸው ግፊት-ብቻ ሣይሆን፣ ነገር ግን በገጽታቸውም ፍፁም መሆን እንዳለባቸውን ግፊት ያለባቸው ይመስለኛል፤ ብለዋል ፕሪንስ (Prince)። "ሁሉንም ነገር ማግኘት ትችላላችሁ የሚለው እውን-ያለሆነ እና ጤናማ-ያልሆነ ነገር ነው፤ እንደ የማይችላል-ነገር ነው፣ እና ደግሞ ምንም-አይደለም!" በመጨመርም ሲናገሩ፤ "ስኬታማ-ለመሆን ሁሉም ነገር የላችሁም፤ የምትወዱትን ነገር ማድረግ እና የምታደርጉትን ነገር መውደድ ብቻ-ነው።"

"እንደ ቡድን ጠንካራ-እንደሆኑ ሁሉ፣ የራሳቸውን-ነገርንም ሲይዙ እንደዚያው ጠንካራ ናቸው፤" ብለዋል ሚስ ጄሲ (Ms. Jess)። "ወደ ማህበረሰቡ ከምርቃታቸው በኋላ ሲቀላቀሉ፣ በሚደርሱበት ማህበረሰብ ውስጥ ሁሉ ለውጥ እንደሚያመጡ አምናለሁ፤ ልክ የእኔን እንደለወጡት-ሁሉ።"

አብዛኛውን-ጊዜ 'WOTF' በየሁለት ሣምንት ባለው ማክሰኞ ቀን ከትምህርት ቤት በኋላ የሚገናኙ እና አዲስ አባላቶችንም - ይቀበላሉ። ተማሪዎች መመዝገብ የሚችሉ እና ተጨማሪ ለመረዳት በካንቫስ (Canvas) ላይ መመዝገብ ይችላሉ።

## መረጃ-ማግኘት(Information) = መከላከያ-ማድረግ (Prevention): በአደንዛዥ ዕፅ አለአግባብ መጠቀም - መከላከል-ላይ፣ የACPS የፀደይ (Spring) 2023 አውደ-ጥናቶች



ልጅዎ ዕፅ ወይም አልኮል-መጠጥ እየተጠቀመ-ከሆነ፤ እንዴት ለይቶ-ማወቅ ይቻላል? የት-መመልከት እንዳለባችሁ ታውቃላችሁ? ምን-መመልከት እንዳለባችሁ ታውቃላችሁ? የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ በዚህ ፀደይ (spring) ወቅት ውስጥ - ስለሚከተሉት ለማወቅ - ከ'የተማሪ አገልግሎቶች እና ፍትሃዊነት-እኩልነት (Student Services and Equity)' እና ከACPS የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ተሣትፎ (Family and Community Engagement (FACE) ማዕከል ጋር አብሮ-ለመቀላቀል፤ ወላጆችን፣ አሳዳጊዎችን እና እንክብካቤ-ሰጪዎችን - ይጋብዛል።

- በአሁኑ-ጊዜ እየተካሄደ ያለው ዕፅ-ዓይነት።
- የአደንዛዥ ዕፅ አለአግባብ-መጠቀም፣ ዓይነቶች እና ምልክቶች።
- መገኘት-የሚችሉ የመረጃ-ምንጮች።

ይህ አውደ-ጥናት የተዘጋጀው - ከ6-12 ክፍሎች ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች ቤተሰቦችን - የተዘጋጅ-ነው። ACPS - ይህን አውደ-ጥናት፣ በፀደይ (spring) ወቅት ውስጥ፣ ሦስት ጊዜ የሚያቀርብ-ይሆናል። በእያንዳንዱ ክፍለ-ጊዜ ውስጥ፣ አንድ-ዓይነት መረጃ የሚሰጥ-ይሆናል። አውደ-ጥናቱ የሚካሄደው በፍሬዲ ማርቲኔዝ (Fredy Martinez) - የACPS ከK-12 የአደንዛዥ ዕፅ አለአግባብ-መጠቀም አገልግሎቶች አስተባባሪ፣ ከ'U.S. Drug Enforcement Administration's Diversion Control Division'፣ ከ'ACPS FACE Center'፣ ከ'Office of Student Support Teams' እና ከ'Office of Safety and Security Services' ከሚገኝ-የትብብር እርዳታ ጋር ተመርቶ-የሚዘጋጅ-ነው። እባካችሁ፣ ቀን-ምረጡ እና በ'ParentSquare' አማካኝነት ተመዝገቡ/sign up አድርጉ።

**ሮብ፣ ማርች (March) 22 ቀን**
ከ6:30-8 p.m.
የዙም ማገናኛ (Zoom link)ን ለመቀበል፤ እባካችሁ ተመዝገቡ/sign up አድርጉ።
* ይህ የርቀት/virtual ክፍለ-ጊዜ በስፓኒሽ የሚካሄድ ሲሆን፤ ከእንግሊዘኛ ትርጉም-አገልግሎት ጋር ይሰጣል።
* የACPS ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ - ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt፣ በዚህ ዝግጅት ላይ ንግግር-በማድረግ - ተከታታይ-ዝግጅቶቹን በማስጀመር-ላይ እርዳታ ያደርጋሉ።
* ይህ ክፍለ-ጊዜ፣ በቀጥታ-ስርጭት በFacebook አማካኝነትም ይሰራጫል።

**ሐሙስ፤ ማርች (March) 30 ቀን**
ከ6:30-8 p.m.
ፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ (Francis C. Hammond) መካከለኛ (Middle) ደረጃ ትምህርት ቤት - ካፊቴሪያ
4646 Seminary Road

* የፒዛ (Pizza) እራት ይቀርባል፤ እና መገኘታቸውን-ላሳወቁ (RSVP -ላደረጉ) ውሱን-የሆነ በቦታው ላይ የሚሰጥ የልጅ-እንክብካቤ/childcare ይኖራል። እባካችሁ፣ [ተመዝገቡ/sign up አድርጉ]።
* ይህ ክፍለ-ጊዜ በእንግሊዘኛ የሚካሄድ ሲሆን፤ በበርካታ-ቋንቋ የትርጉም-አገልግሎቶችም በቦታው-ላይ ይሰጣል።
* ይህ ክፍለ-ጊዜ፣ በቀጥታ-ስርጭት በ[Facebook] አማካኝነትም ይሰራጫል።

**ረቡዕ፣ ኤፕሪል (April) 19 ቀን**
ከ6:30-8 p.m.
የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School)- ኪንግ ስትሪት ካምፓስ (King Street Campus) የካፌቴሪያ
3330 King Street
* የፒዛ (Pizza) እራት ይቀርባል፤ እና መገኘታቸውን-ላሳወቁ (RSVP -ላደረጉ) ውሱን-የሆነ በቦታው ላይ የሚሰጥ የልጅ-እንክብካቤ/childcare ይኖራል። እባካችሁ፣ [ተመዝገቡ/sign up አድርጉ]
* ይህ ክፍለ-ጊዜ በእንግሊዘኛ የሚካሄድ ሲሆን፤ በበርካታ-ቋንቋ የትርጉም-አገልግሎቶችም በቦታው-ላይ ይሰጣል።
* ይህ ክፍለ-ጊዜ፣ በቀጥታ-ስርጭት በ[Facebook] አማካኝነትም ይሰራጫል።

## በሁለተኛው ዓመታዊ የአሌክሳንድርያ ከተማ - አስፈላጊ-የሆኑ ሠራተኞች (Essential Workers)ን ማመስገኛ ሣምንት ላይ፣ ጎልተው-የታዩት/Highlights



ሁለተኛው ዓመታዊ የአሌክሳንድርያ ከተማ አስፈላጊ-የሆኑ ሠራተኞች (Essential Workers)ን ማመስገኛ ሣምንት፤ ትልቅ-ስኬት የተገኘበት ነበር። የአንድ-ሣምንት እርዝመት ያለው አከባበር ላይ ጎልተው-የታዩት - ማክሰኞ ማርች (March) 14 ቀን 2023 ላይ - በፓሪክ ሄንሪ ከK-8 ትምህርት ቤት (Patrick Henry) ውስጥ በተዘጋጀው ልዩ ዝግጅት-ላይ ነው። የክፍሉ/Division እና የከተማ አመራሮች፤ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ - ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt፣ የከተማ ምክር-ቤት ምክት ከንቲባ ኤሚ ቢ. ጃክሰን (Amy B. Jackson)፣ የትምህርት ቤት ሹም እና የማህበረሰብ ግንኙነቶች ኃላፊ ጁሊአ በርጎስ (Julia Burgos)፣ የተቋማት እና ክንውኖች/Facilities and Operations ሹም - ዶ/ር አሊሲአ ሃርት (Dr. Alicia Hart) እና የአሌክሳንድርያ ፒቲኤ ካውንስል (Alexandria PTA Council (PTAC) ፕሬዚዳንት ሚሲ ኢስታብሩክ (Missy Estabrook)፤ እነዚህን ሁሉ ጨምሮ፤ የፓትሪክ ሄንሪ (Patrick Henry) ርዕሰ-መምህርን ዶ/ር ኢንግሪድ ባይነም (Dr. Ingrid Bynum)፣ ተማሪዎች እና ሠራተኞች የተቀላቀሉ እና ለአስተማሪዎቻችን፣ የጤና እንክብካቤ ባለሞያተኞቻችን፣ የእሳት-አደጋ ሠራተኞቻችን፣ የፖሊስ ሹሞችን፣ የአውቶቡስ ሹፌሮቻችንን፣ አገልግሎት-ሰጪዎች (custodians)ን፣ የህንፃ ኢንጂኒየሮችን እና ሌሎች ያላቸውን-ሁሉ ማህበረሰቡን ለመርዳት ለሚያውሉ ባለሞያተኞችን - እናመሰግናለን ለማለት-ተቀላቅለው ነበር።

"ሁሉም አስፈላጊ-የሆኑ ሠራተኞቻችን፣ ACPS ጥራት-ያለው እና በፍትሃዊነት ትኩረት ያደረገ ትምህርትን ለሁሉም ተማሪዎቻችን ለመስጠት እንዲችል - ወሳኝ-የሆኑ ሚናዎችን ይጫወታሉ፤" ብለዋል የACPS ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ - ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt)። "አስፈላጊ-የሆኑ ሠራተኞቻችን (essential workers)፣ በእውነት ከሚገባው-በላይ የሚደነቁ እና ለሁሉም ተማሪዎቻችን እንደ አነሳሽ-መንፈስን የሚሰጡዋቸው ናቸው።"

ለፓትሪክ ሄንሪ (Patrick Henry) ተማሪ የተሰራ የባነር/banner ምልክት - ለሁሉም አስፈላጊ-የሆኑ ሠራተኞች ምስጋናን-ለማሳየት ተለጥፎ ነበር። የተማሪ አምባሳደሮች እና የደህንነት-ጥበቃ ሠራተኞች - በትምህርት ቤቱ ውስጥ - በዋናው-መግቢያ የእንግዳ-መቆያ/main lobby ላይ ሙዚቃ-ከሚጫወቱ ጋር በመሆን፤ እንግዶችን ተቀብለዋል። ክብረ-በዓሉን በመቀላቀል፤ የመዋዕለሕፃናት ተማሪዎች - በርካታ አስፈላጊ-የሆኑ ሠራተኞች የሚለብሷቸውን ልዩ ሰደሪያዎች/vests ለብሰው ያላቸውን ክብር-ለማሳየት - በአካባቢያችን ከሚገኙት በርካታ አስፈላጊ-የሆኑ ሠራተኞቻችን (essential workers) መካከል የአንዳንዶቹን በመወከል ያደረጉ እና ለእነርሱ-የተዘጋጀ መዝሙርንም አቅርበዋል። ተማሪዎች የዳንስ-ማስታወሻን ያቀረቡ እና የእናመሰግናለን/thank-you ካርዶችን በማቅረብ፣ ከክቡር እንግዶች ጋር ተጋርተውም-ነበር። ከማህበረሰባችን አጋር የሆነው የ[Life Enrichment Center](#) ፕሬዚዳንድ ትና መስራች በሆነው በኬቨን ትሩፒን (Kevin Turpin) ስፖንሰር-የተደረገው የምሣ-ዝግጅትም፤ ለአስፈላጊ-የሆኑ ሠራተኞቻችን (essential workers) - እንደ የፕሮግራሙ ክብር-መስጫ ሆኖ - በዝግጅቱ ለተካፈሉ ቀርቦ-ነበር።

የዚህን ዝግጅት ጎልቶ-የሚታዩትን ነገሮች፤ በ[አጭር እና አስደሳች ቪዲዮአችን](#) ውስጥ በመመልከት-ተደሰቱ። የ#ThxACPSEssentialWorkersን በ[Facebook](#), [Twitter](#) እና [Instagram](#) ላይ፣ ግሩም-የሆኑትን ጥቂት አስፈላጊ-የሆኑ ሠራተኞቻችንን - በዓምንቱ ውስጥ እንዴት ማህበረሰባችን እንዳከበራቸው - ተመልከቱት።

## ከተማው፤ በመጪው 'በደህንነት ወደ ትምህርት ቤት በእግር-መሄጃ መንገዶች/Safe Routes to School Walk Audits' ላይ የማህበረሰቡን አስተያየት ለማግኘት ይጋብዛል




የአሌክሳንድርያ ከተማ፤ በእግር መሄድ እና በብስክሌት ሁኔታዎች ላይ በአምስት ትምህርት ቤቶች ዙሪያ - እንደ [Safe Routes to School Program](#) ማካሄጃ አንዱ-አካል አድርጎ፣ ልጆች ወደ ትምህርት ቤት በደህንነት በእግር-እንዲሄዱ እና በብስክሌት እንዲጓዙ ለማድረግ፤ የማህበረሰቡን አስተያየት እየጠየቀ ይገኛል። አምስቱ፣ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ቦታዎች የሚከተሉት ናቸው:

- የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School) - ኪንግ ስትሪት ካምፓስ (King Street Campus)።
- የአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School) - ሚኒ ሃዋርድ (Minnie Howard) Campus።
- ፈርዲናንድ ቲ. ዴይ (Ferdinand T. Day) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት።
- የፍራንሲስ ሲ. ሃመንድ (Francis C. Hammond) መካከለኛ (Middle) ደረጃ ትምህርት ቤት።
- ጆርጅ ዋሽንግተን (George Washington) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት።

ቤተሰቦች፣ ተማሪዎች፣ የትምህርት ቤት ሠራተኞች እና አስተዳዳሪዎች፤ እንዲሁም በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት አቅራቢያ የሚኖሩ ወይም የሚሰሩ ሰዎች በሙሉ፤ ያላቸውን አስተያየት እንዲያጋሩ ይበረታታሉ። እስከ ኤፕሪል (April) 2 ቀን 2023 ድረስ፤ [የኦንላይን የአስተያየት (feedback) ቅጽን](#) ሞልታችሁ-አጠናቅቁ። ቅጹ፤ በእንግሊዘኛ፣ በስፓኒሽ፣ በአማርኛ እና በአረብኛ ቋንቋዎች ይገኛል።

እነዚህ - በእግር-መሄዳውን መገምገሚያ ሂደት (walk audits)፤ ከማህበረሰቡ አስተያየት ጋር በተጨማሪ ሆኖ፣ በእነዚህ አምስት ትምህርት ቤቶች ዙሪያ ስለሚደረገው የደህንነት ማሻያያዎች - ሃሳቦችን በማቅረብ ላይ የሚውል-ይሆናል። ይህ ፕሮጀክት፣ በከተማው የደህንነት ወደ ትምህርት ቤት በእግር መጓዣ ግምገማ ጥረት ውስጥ የሁለተኛው-የሂደት እርምጃ-ነው። የመጀመሪያው የ‘walk audits’ የሂደት-እርምጃ ለ13 የACPS የመጀመሪያ-ደረጃ እና ከK-8 ትምህርት ቤቶች - በ2017 ዓም ተጠናቅቆ-ነበር። ከተማው፣ ከእነዚህ ‘walk audits’ የሚገኙትን-አስተያየቶችን በንቃት-እያስፈጸመ የሚገኝ፣ እና በግምት ከ250 የተሰጡ-አስተያየቶች ውስጥ ከግማሽ-በላይ የሚሆኑት - ወይ ተጠንቅቀው-የሚገኙ አሊያም-ደግሞ በአሁኑ-ጊዜ በሂደት ላይ የሚገኙ ናቸው።

## ለክልላዊ ሽልማት - የACPS ትምህርት-ሰጪን በእጩነት-ማቅረብ




ግሩም-የሆነን የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ትምህርት-ሰጪን - ለNorthern Virginia Magazine’s 2023 Teacher of the Year Award እንደ-እጩነት ማቅረብ። ለዚህ ስመ-ጥር ለሆነ ዓመታዊ ሽልማት፤ መጽሔቱ እጩዎችን እየተቀበለ ይገኛል እና፣ ይህ ሽልማት የሚገባቸውን የአስተማሪዎችን ስሞችን፣ የACPS ማህበረሰብ እንዲያስገባ ያበረታታል።

የትምህርት ቤት አስተዳደሮች፣ አስተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ ተማሪዎች፣ የቀድሞ-ተማሪዎች፣ እና አጠቃላይ ሕዝቡ - ላሳዩት-ትጋት ክብር ማግኘት አለባቸው ብለው የሚያምኑትን አስተማሪዎች በእጩነት ማቅረብ-ይችላሉ። የዓመቱ ምርጥ አስተማሪን በእጩነት-ማቅረቢያውን የማስገቢያው ቀን፤ እስከ አርብ፣ ኤፕሪል (April) 14 ቀን 2023 ድረስ፤ በየኦንላይን ማስገቢያ ቅጽ አማካኝነት የሚገባ-ነው።

የዓመቱ ምርጥ አስተማሪ፤ $10,000 ሽልማት እና ስለእነርሱ የጽሁፍ መግለጫ - በኦክቶበር (October) 2023 - የ‘Northern Virginia Magazine’ እትም ውስጥ የሚካተት-ይሆናል። የመጨረሻ-አሸናፊ የሆኑትም፤ በመጽሄቱ ጽሁፍ ላይ ሽፋን-የሚሰጣቸው ይሆናል።

# ማስታወሻ: የ2023-24 የርቀት-መማሪያ (Virtual Learning) መጠየቂያ ቅጽ፤ እስከ ማርች (March) 24 ቀን 2023 ድረስ - ክፍት-ነው



ሁሉም የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤት (Alexandria City Public School (ACPS) ቤተሰቦች - ለመጪው የትምህርት ዓመት፣ ለልጆቻቸው - የርቀር/virtual መማርን የመጠየቅ ዕድል-አላቸው። ይህን ጥያቄ ለማቅረብ-የሚፈልጉ ቤተሰቦች፤ ተሞልቶ የተጠናቀቀውን የርቀት ትምህርት (virtual learning) መጠየቂያን ሞልተው-ማስገባት አለባቸው፤ ልጁ በርቀት መማር (virtual learning) ውስጥ - በ2023-24 የትምህርት ዓመት ውስጥ መሳተፍ-እንዲችል ለማድረግ፤ እስከ ማርች (March) 24 ቀን 2023 ድረስ ማስገባት አለባቸው።

ይህ የጊዜ-አቀማመጥ - ትምህርት ቤቶች የቤተሰብን ጥያቄዎች ለመመልከት፣ ቤተሰቦችን ስለ እያንዳንዱ ፍቃድ-ያገኘ ወይም የተከለከለ ውሳኔ ማነጋገር እንዲቻል እና በርቀት የበልግ (fall) ተርም/term ውስጥ ለመመዝገብ በቂ-ጊዜ እንዲኖር ያደርጋል። ከዚህ ቀደም በርቀት መማሪያ (virtual learning) ውስጥ ተሳትፈው-የነበሩ እና በቀለም-ትምህርት ሲቸገሩ-የነበሩ ተማሪዎች፤ በመጪው-የትምህርት ዓመት፣ ወደ  የርቀት መማሪያ (virtual learning) ውስጥ እንዲገቡ ዕድል ላይሰጣቸው ይችላል። ለ2023-2024 የርቀት (virtual) መማር ውስጥ መግባትን መርጠው - ቤተሰቦች የሚጠይቁት፤ ሙሉውን-ዓመት ለመሣተፍ-ዓላማ አድርገው ነው፤ ሆኖም ግን፣ ከተማሪው ውጤታማነት ጋር ተያያዥ በሆኑ-ምክንያቶች የተነሳ፤ የተማሪውን ስኬት በተሻለ-መንገድ ለመደገፍ-ሊነሱ የሚችሉ፣ ACPS - የመማር አካባቢውን ለመቀየር ጥያቄ-ሊያቀርብ የሚያስችለው ሁኔታ ሊፈጠር-ይችል ይሆናል።

በ2023-24 የትምህርት ዓመት ወቅት ውስጥ፣ በርቀት ማመሪያ (virtual learning) ውስጥ የሚሳተፉ ከK-5 ክፍሎች ውስጥ ያሉ የ'ACPS' ተማሪዎች፤ የስቴት-ፕሮግራምን በኦንላይን የትምህርት አሰጣጥ አማካኝነት በስቴቱ-ሙሉ በሚሰጠው በVirtual Virginia አማካኝነት፣ በመደበኛ-መልኩ (synchronous) የሚሰጥ ኮርሶችን ይወስዳሉ። ከ6-12 ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች፤ መደበኛ-ባልሆነ መንገድ የሚሰጥ (asynchronous) ኮርሶችን በEdgenuity አማካኝነት የሚወስዱ ሲሆን፣ ይህም የኦንላይን ኮርሶችን እና የትምህርት አሰጣጥ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ነው። የርቀት ኮርሶች (Virtual courses)፣ የተጠናከረ ንባብ የሚያካሂዱ እና፣ በክፍል-ደረጃ ላይ በሆነ-ችሎታ ማንበብ እንዲችሉ፣ የተማሪዎችን ስኬት በጥሩ ሁኔታ ለማረጋገጥ፣ በርቀት ኮርሶች (virtual courses) እንዲካፈሉ ይመከራል።

የርቀት-መማሩ ለተማሪዎ ተገቢ-ሊሆን ስለመቻልና-አለመቻሉን ማንኛውም-ጥያቄዎች ካሏችሁ፤ እባካችሁ - የተማሪውን የትምህርት ቤት ካውንስለር አነጋግሩ። ዕለታዊ የርቀት መማር የጊዜ-ሰሌዳዎችን ናሙና ለማየት፤ እባካችሁ ከዚህ-በታች ያሉትን ማገናኛዎች/links ጎብኙ:

- የመጀመሪያ-ደረጃ: (ከK-5 ክፍሎች) የክፍል የርቀት መማር (Virtual Learning) የጊዜ-ሰሌዳ ናሙና
- ሁለተኛ-ደረጃ: (ከ6- 12 ክፍሎች) የክፍል የርቀት መማር (Virtual Learning) የጊዜ-ሰሌዳ ናሙና

ስኬታማ የሆኑ የርቀት/virtual ተማሪዎች፤ የሚከተሉትን የርቀት ትምህርት (virtual learning) የመማር-ባህሪያቶችን ማሳየት አለባቸው:

- የክፍል-ደረጃን የጠበቀ ንባብ: የርቀት የኮርስ-ስራ፣ በተወሰነ ከማንበብ ደረጃ ጋር ግንኙነት-እንዲኖረው የተደረገ የርቀት ኮርስ የቀረበ-ነው። ስለሆነም፤ ተማሪዎች የክፍል-ደረጃቸውን የጠበቀ ንባብ እንዲኖራቸው ይመከራል።
- የራስ-ተነሳሽነት: ከ6-12 ክፍል ደረጃ ላይ ለሚገኙ በራሳቸው የተመራ-የመማር ሂደትን ማካሄዳ አንዳንድ ችሎታዎች ሊኖራቸው ያስፈልጋል። ከK-5 ክፍሎች ውስጥ የሆኑ ተማሪዎች፤ በመኖሪያ-ቤት ውስጥ ከአዋቂ-ሰው እርዳታ ሊያስፈልጋቸው-ይችላል።
- እራስን-ችሎ መማር-የሚችል (Independent Learner): የርቀት መማር አካባቢው፤ ተማሪዎች በራሳቸው የእርምጃ-ጉዞ ለመማር ያስችላቸዋል፤ ግን የተወሰኑ የማብቂያ-ጊዜ ውስጥ መግባት ያለባቸውን ማሟላት አለባቸው።
- የጊዜ-አጠቃቀም: የርቀት ኮርስ-ስራ፣ ልክ እንደ በአካል-ተገኝቶ መማሩ-ሁሉ፣ ዕለታዊ ስራ ያስፈልገዋል። ተማሪዎች፤ በኮርሱ የእርምጃ-ፍጥነት ላይ ለመቆየት እንዲችሉ፤ በቀኑ ውስጥ በቂ የሆነ-ጊዜ መመደብ አለባቸው።
- በትክክል-የታየ፣ በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (Attendance): ተማሪዎች - በአካል-ተገኝቶም ሆነ በርቀት/virtual አካባቢ-ውስጥ በሚማሩ-ጊዜ፤ የሚፈለገው በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (attendance) መዝገብ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።
- በትክክል-የታየ፣ ስራን የማጠናቀቅ ችሎታ: ተማሪዎች - በአካል-ተገኝቶም ሆነ በርቀት/virtual አካባቢ-ውስጥ በሚማሩ-ጊዜ፤ የሚፈለገው በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (attendance) መዝገብ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።
- የኮምፒውተር ትምህርት: ከፍተኛ-ደረጃ ያለው የኮምፒውተር ችሎታ አስፈላጊ-አይደለም፤ ነገር-ግን - ተማሪዎች - ኢሜል፣ ኢንተርኔት እና መሠረታዊ የኪቦርድ-አጠቃቀም ችሎታዎች - የማከናወኛ እውቀት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።
- ብቃት-ያለው የጽሁፍ ግንኙነት ማድረጊያ ችሎታዎች - ለሁለተኛ-ደረጃ: በርቀት ትምህርት ውስጥ የሚገቡ ተማሪዎች፣ ግንኙነት/communicate ለማድረግ እና የቤት-ስራዎችን ለማጠናቀቅ - ግልጽ-በሆነ ሁኔታ መፃፍ የሚችሉ- መሆን አለባቸው።

ለመጪው የትምህርት ዓመት 2023-24፣ ለተማሪዎ የርቀት መማር/virtual learningን ለመምረጥ የምትፈልጉ-ከሆነ፤ እስከ ማርች (March) 24 ቀን 2023 ድረስ፣ የርቀት መማሪያ/virtual learning - መጠየቂያ ቅጹን፣ እባካችሁን - ሞልታችሁ አጠናቅቁ።

## ለማርች 16 ቀን 2023 - የትምህርት ቤት ቦርድ ማጠቃለያ (Summary)



በዚህ በማርች (March) 16 ቀን 2023 ስብሰባ ላይ፣ የትምህርት ቤት ቦርድ - "Simply the Best" የሚለውን አቀራረብ/presentation፣ ከጆርጅ ዋሽንግተን (George Washington) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ያገኘ እና የሚከተሉትን ርዕሶች-ምላሽ ሰጥቷል:

- ወርሃዊ የተቋማቶች የሪፖርት አጠቃቀም።
- ለSY2023-24 የቀለም-ትምህርት የቀን-መቁጠሪያዎች (Academic Calendars) ከለሳ-ማድረጊያ ሃሳብ-ቀርቧል።
- የጦር-መሣሪያዎችን የመቀነስ የፓየት ሃሳብ--ማቅረቢያ--የመጨረሻ ማሻሻይ/update።

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ አጀንዳዎችን እና ሰነዶችን ለማግኘት፤ Electronic School Boardን ይጎብኙ። ስብሰባዎችን በቀጥታ ለመመልከት እና ለመካፈል እንዴት እንደሚችሉ መረጃዎችን ለማግኘትም፤ በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ድህረ-ገጽ መጎብኘት ትችላላችሁ።

# በማርች (March) 9 ቀን 2023 ላይ፣ የአሌክሳንድርያ የCOVID-19 ማህበረሰብ ያለበት-ደረጃ




እስከ ማርች (March) 9 ቀን 2023 - ባለው-ጊዜ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የCOVID-19 ማህበረሰቡ-የሚገኝበት ደረጃ - ዝቅተኛ/low ሲሆን፤ ባለፉት ሰባት ቀናቶች ውስጥ፤  በየ100,000 ሰዎች፣ 35.75 ታማሚዎች አሉት። የበለጠ ለማወቅ፤ [Alexandria COVID-19 dashboard] ጎብኙ።

የመረጃ-ስብስቡ (data)፤ በመጨረሻ-እንዲስተካከል የተደረገው በማርች (March) 9 ቀን 2023 ላይ እንደሆነ፣ እባካችሁ አስታውሱ። የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት (Centers for Disease Control and Prevention)፤ በሦስት ሜትሪክስ (three metrics) ጥምሮች ውስጥ - የCOVID-19 የማህበረሰብ የደረጃ-መጠንን ለመወሰን ተመልክቷል: አዲስ የCOVID-19 ታማሚ ሆነው የተመረመሩበትን በ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ፤ ገብተው-የተኙ በCOVID-19 ታካሚዎች የተያዙ አልጋዎች - በእያንዳንዱ የCOVID-19 በሽተኛ-ቁጥር፤ እና አጠቃላይ አዲስ የCOVID-19 ታማሚዎችን በየ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ-ይመለከታል።